# የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 5/2002 ዓ.ም. (የተሻሻለው)

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀፅ 1. አውጭው ባለስልጣን**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም. አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 19 እና አንቀፅ 110 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥ...ል።

**አንቀፅ 2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 5/2002 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀፅ 3. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።

2. "የምርጫ ህግ" ማለት የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም. ነው።

3. "ጠቅላላ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክZ ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።

4. "የአካባቢ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክZ ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።

5. "ማሟያ ምርጫ" ማለት በይውረድልን ወይም በማንኛውም ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ የተጓደሉ

የምክZ ቤት አባላት መቀመጫዎችን ለማሟላት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡

6. “ድጋሚ ምርጫ” ማለት በምርጫ ሕጉ መሠረት በርዱ ድጋሚ ምርጫ እንዲያካሂድ ሲወስን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት በማይቻልበት ጊዜ የሚካሄድ ምርጫ ነው።

7. “ህዝበ ውሳኔ” ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገመንግሥት መሰረት ሲወሰን የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት እና የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ ድምፅ የሚሰጥበት ስርዓት ነው፡፡

8. “የምርጫ ክልል” ማለት ለምርጫ አፈፃፀም እንዲያመች እና ህዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በሕግ መሠረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው።

9. “የምርጫ አስፈፃሚ” ማለት በቦርዱ እና በየደረጃው ለሚካሄድ ምርጫ በተቋቋሙ ምርጫ ጽሕፈት ቤቶች በቋሚነት፣ በኮንትራት ወይም በጊዜያዊነት ምርጫን የሚያስፈፅም ሰው ነው፡፡

10. “የህዝብ ታዛቢ” ማለት በእያንዳንዱ ምርጫ ክልል እና ምርጫ ጣቢያ ምርጫን እንዲታዘቡ በህዝብ የሚመረጡ ገለልተኛ የአካባቢ ነዋሪዎች ናቸው፡½

11. “እጩ” ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፖለቲካ ድርጅት ወይም በግሉ በምርጫ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ ሰው ነው፡፡

12. “ተቀማጭ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ የሚወከልና በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ ተቀምጦ የምርጫ ሂደትንና የወከለውን አካል መብት መከበርን የሚከታተል ሰው ነው፡፡

13. “ተንቀሳቃሽ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል እጩ ተወክሎ በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች እየተንቀሳቀሰ የምርጫ ሂደትንና የወከለውን

ድርጅት ወይም የግል እጩ መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

14. "የምርጫ ፀጥታ አስከባሪ" ማለት በምርጫ ወቅት በምርጫ ጽሕፈት ቤቶች እና በምርጫ ጣቢያዎች ላይ የምርጫ ፀጥታ እንዲያስከብሩ የሚመደቡ የፖሊስ ወይም የአካባቢ ሚሊሽያ ወይም ደንብ አስከባሪዎች ናቸው፡½

15. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**አንቀፅ 4. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚካሄድ የጠቅላላ ምርጫ፣ የአካባቢ ምርጫ፣ የድጋሚ ምርጫና የማሟያ ምርጫ እንዲሁም እንዳግባብነቱ በህገመንግሥቱ መሰረት ለሚካሄድ ሕዝበ ውሣኔ ተፈፃሚ ይሆናል፡½

**አንቀፅ 5. አላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1. የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች እና ሌሎች ለምሳሌ ተንቀሳቃሽ ወኪል፣ የሀገር ውስጥና የአለም አቀፍ ታዛቢዎች አካላት በድምፅ አሰጣጡ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ ላይ ወጥነት ያለው አሠራር እና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው።

2. የድምፅ አሰጣጡን፣ ቆጠራውን እና የውጤት አገላለፅ ሂደት አፈፃፀሙን ግልፅ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ነው፡፡

**አንቀፅ 6. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለድምፅ አሰጣጥ

### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ቅድመ ዝግጅት

## አንቀፅ 7. የምርጫ አፈፃፀም ስልጠና

የምርጫ ጣቢያው ምርጫ አስፈፃሚዎች፡-

1. በምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳው እና ቦርዱ በመገና’ ብዙሃን በሚያወጣው መግለጫ መሠረት በምርጫ ክልል የሚሰጠውን የምርጫ አፈፃፀም ስልጠና በአካል በመገኘት መከታተል፣

2. ቦርዱ ስለድምፅ አሰጣጥ፣ ስለድምፅ ቆጠራና ስለውጤት አገላለፅ ለምርጫ አስፈፃሚዎች በተለያዩ የመገና’ ዘዴዎች የሚሰጠውን ስልጠና መከታተል

አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 8. ለምርጫ ጣቢያው መራጭ ህዝብ የሚሰጥ ገለፃ

1. የምርጫ ጣቢያው ምርጫ አስፈፃሚዎች ምርጫ ጣቢያው ለመራጭ ሕዝብ በምርጫ ጣቢያው ስለሚሰጠው ገለፃ ፕሮግራም በማውጣት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋሉ፡፡
2. ለመራጩ ሕዝብ የሚደረገው ገለፃ፡-

ሀ. የድምፅ መስጫውን ቀን፣

ለ. የምርጫ ጣቢያው የሚከፈትበትና የሚዘጋበትን ሰዓት፣

ሐ. መራጩ በድምፅ መስጫው ዕለት የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይዞ መምጣት እንዳለበት፣

መ. የሚካሄደው የምርጫ ዓይነት እና የድምፅ መስጫ ወረቀት ዓይነት፣

ሠ. አንድ መራጭ ለየምርጫው ዓይነት ለምን ያህል ዕጩ ድምፅ መስጠት እንደሚችል እና እንዴት ድምፅ መስጠት እንዳለበት፣

ረ. የድምፅ አሰጣጡን፣ የድምፅ ቆጠራውንና ወ"ጤት አገላለፁን አጠቃላይ ሂደት፣

ሰ. ወደምርጫ ጣቢያው ማስገባት የሚከለከሉ ነገሮችንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በዝርዝር

ማካተት አለበት፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 ከተዘረዘረው በተጨማሪ መራጩ ህዝብ ለየምክZ ቤቱ አባላት ምርጫ የቀረቡ ዕጩዎች፡-

ሀ. ብዛትና ስም ዝርዝራቸውን፣

ለ. የወከላቸውን የፖለቲካ ድርጅት ስም፣

ሐ. በግል የቀረቡ ከሆነ የግል ዕጩ መሆናቸው

መ. የመረጡትን የመወዳደሪያ ምልክ}

እንዲያውቀው በግልፅ ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

## አንቀፅ 9. ለህዝብ ታዛቢዎችና ለተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች ስለሚሰጥ ገለፃ

የምርጫ ጣቢያው ምርጫ አስፈፃሚዎች፡-

1. ለምርጫ ጣቢያው የህዝብ ታዛቢዎች፣ ለተቀማጭ የዕጩ ወኪሎችና ለምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች፡-

ሀ. ስለድምፅ አሰጣጡ፣

ለ. ስለድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ፣

ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት አለባቸው።

2. እያንዳንዱ የህዝብ ታዛቢ፣ ተቀማጭ የዕጩ ወኪል ወይም የምርጫ ፀጥታ አስከባሪ በሂደቱ ስለሚኖረው ተግባር እና ኃላፊነት በዝርዝር ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀፅ 10. የምርጫ ጣቢያ ዝግጅት

1. የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት መራጩ ህዝብ ድምፅ የሚሰጥበት የምርጫ ጣቢያ ምቹና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ በምርጫ አስፈፃሚዎች መዘጋጀት አለበት፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርጫ ጣቢያውን ቅጥር ግቢ በሀገሪቱ እና በክልሉ ባንዲራ እንዲሁም በርዱ በሚያሰራጨው የሚለጠፉ ፖስተሮች በተገቢው ሁኔታ ማዘጋጀት አለበት፡፡

3. የድምፅ አሰጣጡን ሂደት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል ቦርዱ በሚያሰራጨው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስዕላዊ መግለጫ መሰረት፣

   ሀ. ድምፅ በሚስጥር የሚሰጥበት ቢያንስ ሁለት የሚስጥር ድምፅ መስጫ፣

   ለ. የድምፅ መስጫ ኮሮጆ የሚሰቀልበትን ወይም የሚንጠለጠልበትን፣

   ሐ. በድምፅ መስጫው መግቢያ አካባቢ ለመራጩ ስለድምፅ አሰጣጡ ገለፃ የሚሰጥበትን፣

   መ. ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች እና የሕዝብ ታዛቢዎች የሚቀመጡበትና የድምፅ አሰጣጡን ሂደት በግልፅ ለመመልከት የሚችሉበት፣

   ሠ. የመዝገብ ሹሞች የሚቀመጡበት፣ የድምፅ መስጫ ወረቀት ለመራጩ የሚሰጥበትና የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም የሚቀባበት

   ቦታ ተለይቶ መዘጋጀት አለበት።

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ተለይተው የተዘጋጁትን ቦታዎች ለመለየት የሚያስችሉ ከቦርዱ የሚላኩ መለያ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣ መለጠፍ ወይም መሰቀል ይኖርባቸዋል።

5. ለየምርጫው ዓይነት የዕጩዎችን ስም፣ መወዳደሪያ ምልክቶችን እና ፓርቲያቸውን ወይም በግል ተወዳዳሪ መሆናቸውን ማስተዋወቂያ፣ የድምፅ አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ ፖስተሮች ለመራጩ ገለፃ በሚደረግበት ቦታ፣ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ እና ህዝብ በብዛት በሚገኙባቸው ቦታዎች መለጠፍ ወይም መንጠልጠል አለበት።

6. የዕጩዎች ሙሉ ስም እና ሌሎች መረጃዎች በተዘጋጀው ፖስተር ላይ ሲፃፍ በተመሳሳይ ቀለም እና እስክሪቢቶ እንዲሁም በተመሳሳይ የእጅ ጽሑፍ መሆን ይኖርበታል።

7. ለድምፅ ቆጠራው መብራት ባይኖር ወይም በተለያየ ምክንያት ቢቋረጥ እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሻማ፣

ኩራዝ፣ ፋኖስ ወይም ማሾ በቅድሚያ መዘጋጀት ይኖርበታል።

## አንቀፅ 11. የድምፅ መስጫ ወረቀት ዝግጅትና ስርጭት

ቦርዱ፦-

1. ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነት መራጩ በግልፅ ሊረዳው የሚችል እና እስከተቻለ ድረስ ለማጭበርበር የማይመች የድምፅ መስጫ ወረቀት ያዘጋጃል፡፡

2. በአንድ ጊዜ ለተለያዩ ምክZ ቤቶች ምርጫ የሚያዘጋጀው የድምፅ መስጫ ወረቀት ቀለም የተለያየ ይሆናል፡½

3. የዕጩዎች ፎቶግራፍ፣ የዕጩ መለያ ምልክት፣ የእጩዎች ሙሉ ስም ከነአያት እና የፖለቲካ ድርጅታቸው መጠሪያ የታተመበት የድምፅ መስጫ ወረቀት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

4. በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ እና በተጨማሪ ለመጠባበቂያ የሚሆን የተወሰነ ቁጥር ያለው የድምፅ መስጫ ወረቀት ይልካል፡፡

## አንቀፅ 12. የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ርክክብና ጥበቃ

1. የምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳው መሰረት የምርጫ ክልሉ በሚያደርገው ጥሪ በጽሕፈት ቤቱ በአካል በመገኘት ለምርጫ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን ይረከባሉ፡፡

2. ማንኛውም የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ከአንዱ ሰው ወደሌላው በሚተላለፍበት ጊዜ ህጋዊ የርክክr ሥርዓትን ተከትሎ በሰነድ መፈፀም ይኖርበታል።

3. ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራና ለውጤት አገላለፅ አገልግሎት የሚሰጡ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከምርጫ ክልሉ ታሽገው በምርጫ ጣቢያው በመጡበት ሁኔታ እስከ ድምፅ መስጫው ዕለት እሽጉ ሳይፈታ፣ ለጥበቃ አስተማማኝ፣ ከተባይና ከአይጥ በፀዳና እርጥበት በሌለበት ቦታ በጥንቃቄ መቀመጥ አለባቸው።

4. ከእሽጉ ውጭ ያሉት ለምርጫው አፈፃፀም የሚረዱ የሚለጠፉ ፖስተሮች፣ በራሪ ጽሑፎች፣ ማኑዋሎች፣ ስዕላዊ መግለጫዎች እና የመሳሰሉት በምርጫ ጣቢያው ለተላኩለት ዓላማ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

**አንቀፅ 13. ለሚመለከተው አካል ጥሪ ስለማስተላለፍ**

የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የህዝብ ታዛቢዎች፣ ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች፣ የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች ተገቢውን ስልጠና እንዲወስዱ እና በድምፅ መስጫው ዕለት ከንጋቱ 11:00 ሰዓት በተመደቡበት የምርጫ ጣቢያ እንዲገኙ ከአንድ ሣምንት በፊት ጥሪ ያስተላልፋል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የምርጫ ጣቢያ ደህንነትና ሥነ ሥርዓት አጠባበቅ

**አንቀፅ 14. የምርጫ ጣቢያ ደህንነት**

1. የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት ደህንነታቸውና ጥበቃቸው አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ በምርጫ አስፈጻሚዎች መዘጋጀት አለባቸው።

2. የእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የምርጫ ጣቢያውን ደህንነት የማስጠበቅ ሀላፊነት አለበት።

3. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ የምርጫ ጣቢያውንና የአካባቢውን ፀጥታና ደህንነት የሚያስከብሩ የፖሊስ ወይም የፀጥታ አስከባሪዎች እንዲመደቡለት ያደርጋል።

4. በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ደህንነትና ፀጥታ የሚያስከብሩ የፖሊስ ወይም የፀጥታ ኃይሎች ይመደባሉ።

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ለምርጫ ጣቢያው የተመደቡት የፖሊስ ወይም የፀጥታ ሀይሎች በተመደቡበት ቦታ እንዲገኙ አስፈላጊውን ጥሪ ያደርጋል። በተመደቡበት ቦታ በአግባቡ መገኘታቸውንና ተግባራቸውን ለማከናወን ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ህጋዊ የሥራ መመሪያ ይሰጣል።

6. የምርጫ ጣቢያው የሕዝብ ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያውን ደህንነት ለመጠበቅ የፖሊስ ወይም የፀጥታ ኃይል እንደሚያስፈልግ ካመኑ የሚመለከተው አካል እንዲመድብላቸው በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አማካይነት ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

7. የምርጫ ጣቢያ ለምርጫ ከመከፈቱም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጋ በኋላ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከህዝብ ታዛቢዎች ከዕጩ ወኪሎች እና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም፡፡

**አንቀፅ 15. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች ገለፃ**

የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ለምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች ስለሥራቸው ተገቢውን ገለፃ ወዲያውኑ ይሰጣል።

**አንቀፅ 16. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች ተግባርና ኃላፊነት**

1. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ በር ላይ በመሆን መራጩን ህዝብ በቅደም ተከተል በመፈተሽ ወደምርጫ ጣቢያው እንዲገባ ያደርጋሉ፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የሚካሄደው ፍተሻ የሚከናወነው በተመሳሳይ ጾታ መሆን አለበት፡፡

3. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች ወደድምፅ መስጫ ጣቢያው እንዳይገባ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 የተከለከለን ማንኛውንም አይነት ዕቃ ይዞ መግባት የተከለከለ መሆኑን በቅድሚያ በማስረዳት ከመራጩ ላይ ተረክበው በጊዜያዊነት በማስቀመጥ መራጩ ድምፅ ሰጥቶ ሲመለስ በአግባቡ ለባለቤቱ መመለስ አለባቸው፡፡

4. የቦርዱን ፈቃድና መታወቂያ የያዙ የምርጫ ታዛቢዎች፣ ጋዜጠኞች እና ተንቀሳቃሽ ወኪሎች እንዳመጣጣቸው በመፈተሽ ወደምርጫ ጣቢያው እንዲገቡ ያደርጋሉ፡፡

5. የፀጥታ አስከባሪዎች በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት፡-

ሀ. የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ የሌላቸው ሰዎች ወደምርጫ ጣቢያው እንዳይገቡ ከገቡም እንዲወጡ ያደርጋሉ።

ለ. ድምፅ ሰጥተው የጨረሱ ሰዎች ከምርጫ ጣቢያውና ከአካባቢው እንዲርቁ ያደርጋል፡፡

ሐ. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 5 /ሀ/ የተደነገገው ቢኖርም የመራጮች ምዝገባ ካርድ የጠፋባቸው መራጮች ጉዳያቸው እስኪጣራ ለይቶ በማቆየት ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ያሳውቃል፡፡

6. የምርጫ ጣቢያውንና አካባቢውን በስካርም ሆነ በሌላ ምክንያት እንዳያውኩ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡

7. በምርጫ ጣቢያው መግቢያ በርና በአካባቢው የሚሰባሰቡ ሰዎችን በምርጫ ጣቢያው በርና አካባቢ መጨናነቅና ትርምስ እንዳይፈጠር ለማድረግ፡-

ሀ. ድምፅ ያልሰጡ ከሆነ ወደምርጫ ጣቢያው ገብተው ድምፅ እንዲሰጡ ፈትሾ ያስገባል፡፡

ለ. ድምፅ የሰጡ ወይም መራጮች ያልሆኑትን ደግሞ ከአካባቢው እንዲርቁ ያደርጋል፡፡

8. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች ተግባራቸውን ለማከናወን የሚያስቸግር ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ችግሩን ለምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በማሳወቅ የሚሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋሉ።

9. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች የተሰጣቸውን ሀላፊነት በትዕግሥትና በሰላማዊ መንገድ ማከናወን ይገባቸዋል። ሆኖም ችግሩ በሰላማዊ መንገድ ሊፈታ ካልቻለ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ችግሩን ለማስወገድ ተገቢ የሆነውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳሉ።

10. የፀጥታ ጥበቃ አስከባሪዎች የድምፅ አሰጣጡና ቆጠራው በምርጫ ጣቢያው ከተጠናቀቀ በኋላ ለምርጫ ቁሳቁሶች አስፈላጊውን ጥበቃ ማድረግና ወደምርጫ ክልል ሲጓጓዝም አጅበው ማድረስ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀፅ 17. የተከለከሉ ተግባራት

1. ማንኛውም ሰው በምርጫ ጣቢያው 500 ሜትር ዙሪያ ክልል ውስጥ በሰካር፣ መሣሪያ በመያዝ ወይም በሌላ በማናቸውም ፀጥታን በሚያደፈርስ አኳኋን መገኘት የለበትም፡፡

2. መራጭ ያልሆኑና ድምፅ የሰጡ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው 500 ሜትር ክልል ውስጥ መገኘት የለባቸውም።

3. ማንኛውም ሰው ያልፈቃድ ወደምርጫ ጣቢያው በመግባት ወይም በምርጫ ጣቢያው ግቢ ውስጥም ሆነ ውጭ የምርጫውን እንቅስቃሴ ማወክ ወይም ማደናቀፍ የለበትም፡፡

## አንቀፅ 18. ህገወጥ ድርጊትን ስለመከላከል

1. በምርጫ ጣቢያ የተመደቡ የምርጫ ፀጥታ ጥበቃ አስከባሪዎች የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በሚሰጣቸው መመሪያና በሚመድባቸው ቦታ ከምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ እና ውጭ በመሆን የምርጫ ጣቢያውንና የአካባቢውን ፀጥታ በማስከበር ምርጫው በሰላማዊ መንገድ እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከዚህ በላይ በአንቀፅ 17 የተዘረዘሩት የተከለከሉ ተግባራት ሲፈፀሙ ወይም በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ህገወጥ ድርጊት ሲፈፀም የፀጥታ ኃይሎች ወደምርጫ ጣቢያ ውስጥ ገብተው አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወስዱ ማዘዝ ይችላል፡፡

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መግባት የሌለበትን ሰው ወይም የምርጫውን እንቅስቃሴ ያወከ ወይም ለማወክ የሞከረን ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጣ ሊያዝ ይችላል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው የፀጥታ አስከባሪዎች በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ትዕዛዝ ወደምርጫ ጣቢያው ውስጥ በመግባት የፀጥታ ማስከበር ተግባራቸውን ከፈፀሙ በኋላ ወዲያውኑ ከምርጫ ጣቢያው ውስጥ በመውጣት የተመደቡበትን ተግባር ያከናውናሉ፡፡

5. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ማንኛውንም ህገወጥ ሰነድ ይዞ በምርጫ ጣቢያ ስለመገኘቱ አሳማኝ ጥቆማ የቀረበበትን ሰው በዕጩ ወኪሎችና በህዝብ ታዛቢዎች ፊት ለመፈተሽና ድርጊቱ ተፈፅሞ ከሆነ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ይችላል፡፡

**አንቀፅ 19. ወደምርጫ ጣቢያ የማይገቡ ነገሮች**

1. ማንኛውም ሰው የጦር መሳሪያ ወይም እንደጩቤና ሰንጢ የመሳሰሉ ስለትነት ያላቸውን ወይም እንደየአካባቢው ሁኔታ ለሀይል መጠቀሚያነት የሚውሉ እንደዱላ፣ ጉማሬ፣ ቁራጭ እንጨት ወይም ብረት ወይም ሌላ ማንኛውንም ተቀጣጣይ፣ የሚፈነዳ፣ ጠጣር ወይም ፈሳሽ ነገር ይዞ ወደምርጫ ጣቢያ መግባት የለበትም፡፡

2. ከላይ የተዘረዘሩትን የተከለከሉ ነገሮች ወደምርጫ ጣቢያ ይዞ የመጣ መራጭ በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ለምርጫ ጣቢያ የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች በአደራ አስቀምጦ መግባት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## በድምፅ መስጫ ዕለት በቅድሚያ የሚከናወኑ ተግባራት

**አንቀፅ 20. በድምፅ መስጫ ዕለት ስለሚገኙ ሰዎች**

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 መሠረት በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ጥሪ የተደረገላቸው፡-

1. የምርጫ አስፈፃሚዎች
2. የሕዝብ ታዛቢዎች
3. የፖለቲካ ፓርቲና የግል ዕጩ ተቀማጭ ወኪሎች
4. የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች

ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት በምርጫ ጣቢያው በመገኘት የተዘጋጀላቸውን ቦታ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡

**አንቀፅ 21. የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ቁጥጥር**

1. ማንኛውም የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ህጋዊ የርክክr ስርዓትን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ከምርጫ ክልሉ እንደታሸጉ የተረከባቸውን ሰነዶችና ቁሳቁሶች ቀደም ሲል ታሽገው በነበረበት ሁኔታ እሽጉ ሳይፈታ መቆየቱን ለህዝብ ታዛቢዎችና ለተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በግልፅ በማሳየት እሽጉ ተፈትቶ እንዲቆጠር ያደርጋል፡፡

3. የተቆጠሩት ሰነዶችና ቁሳቁሶች ብዛትና አይነት የተሟላና ግ"ድለት የሌላቸው መሆኑን ከመረከቢያ ቅጹ ጋር በማመሳከር ያረጋግጣል፡፡ ልዩነት ካለ በቃለ ጉባኤ ተመዝግቦ ሂደቱ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 22. የመራጮች መዝገብ ቁጥጥር

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የመራጮች ምዝገባ የተከናወነባቸው መዝገቦች፡-

1. ምዝገባው ሲጠናቀቅ በቃለጉባኤ ከተያዘው የመጨረሻ ተመዝጋቢ ቁጥር ውጭ አዲስ ተመዝጋቢ ያልተመዘገበባቸው መሆኑን ወይም

2. ምንም አይነት ስረዛ ያልተከናወነባቸው መሆኑን

3. በአጠቃላይ የመራጮች ምዝገባ ሲጠናቀቅ በነበሩበት ሁኔታ መሆናቸው"

ለሕዝብ ታዛቢዎችና ለተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በግልፅ ካሳየ በኋላ ለየመዝገብ ሹሞች ይሰጣል፡፡

## አንቀፅ 23. ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ስለሚደረግ ጥንቃቄና ቁጥጥር

1. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በእያንዳንዱ የድምፅ መስጫ ወረቀት ጀርባ ላይ በመፈረም እና የምርጫ ጣቢያ ልዩ ማህተም በማድረግ በታዛቢዎችና በተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች ፊት በግልፅ ይቆጥራል።

2. በእያንዳንዱ የመራጮች መዝገብ በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከየምርጫው አይነት በግልፅ ቆጥሮ እና ለያይቶ ለድምፅ መስጫ ወረቀት አዳዩ ያስረክባል፡½

3. የተረፈውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በይፋ በመቁጠር በመጠባበቂያነት ለይቶ ያስቀምጣል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### አንቀፅ 24. የድምፅ መስጫ ኮሮጆ እና የኮሮጆ ቁልፍ ቁጥጥር

የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ፡-

1. የድምፅ መስጫ ኮሮጆ ቁጥርና የሦስቱም ዓይነት የኮሮጆ ቁልፎች ቁጥር የህዝብ ታዛቢዎች፣ ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች በተገኙበት በግልፅ በማሳየት እንዲመዘገብ ያደርጋል፡፡

2. የድምፅ መስጫ ኮሮጆው ባዶ መሆኑንና ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተዘረዘሩት ሰዎች ፊት በማቅረብ በውስጡ ምንም ነገር የሌለ መሆኑ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

3. ባዶ መሆኑ የተረጋገጠው የድምፅ መስጫ ኮሮጆ ለዚሁ በተዘጋጀውና ቀደም ሲል መለያ ቁጥሩ በተመዘገበው አረንጓዴ ቁልፍ የጎኑ ባለሁለት ዚፕ በግልፅ እንዲዘጋ እና እንዲቆለፍ ያደርጋል፡፡

4. የድምፅ መስጫ ኮሮጀው ለህዝብ ታዛቢዎችና ለተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች ፊት ለፊት በግልፅ ሊታይ በሚችልበት ሁኔታ በተዘጋጀው ቦታ ላይ ተወጥሮ እንዲንጠለጠል ያደርጋል፡፡

### አንቀፅ 25. የሌሎች ቁሳቁሶች ዝግጅት

1. በሚስጥር ድምፅ መስጫ ክፍል ውስጥ አንድ እስኪርቢቶና አንድ የጣት አሻራ መርገጫ ይቀመጣል፡፡

2. የሚስጥር ድምፅ መስጫ ክፍሉ ለሁሉም ክፍሎች እስኪርቢቶና የጣት አሻራ መርገጫ ለየራሱ ይቀመጣል፡፡

3. የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም በተገቢው ቦታ ይቀመጣል፡፡

4. የጣት አሻራ መርገጫ በሁለቱ መዝገብ ሹሞች መካከል ይቀመጣል፡፡

### አንቀፅ 26. ዝግጅት መጠናቀቁን ይፋ ስለማድረግ

1. ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት ተግባራት በህጉ መሠረት መፈፀማቸውን እና በምርጫ ጣቢያው ድምፅ አሰጣጡን ለመጀመር የሚያስችል መሆኑ ቦርዱ በአዘጋጀው የመክፈቻ ቃለጉባኤ ቅፅ ላይ ተመዝግቦ የህዝብ ታዛቢዎች፣ ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ይፈራረማሉ፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የምርጫ ጣቢያው መከፈቱንና ድምፅ ሰጪዎችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን የድምፅ አሰጣጡ መጀመሩን ለመራጮች በይፋ ያሳውቃል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የድምፅ አሰጣጥ መጀመር

### አንቀፅ 27. የድምፅ መስጫ ቀን

1. የጠቅላላ ምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ቦርዱ በሚወስነው ቀን በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች በአንድ ላይ ይጀመራል፡፡

2. የአካባቢ ምርጫ ድምፅ አሰጣጥ እንደየምክZ ቤቶቹ ምርጫ አፈፃፀም ሁኔታ አመቺነት ቦርዱ በሚወስነው የተለያዩ ቀና} የሚካሄድ ይሆናል፡½

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም የሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች ስራቸውን በተለየ ቀን እንዲጀምሩ ቦርዱ ሊወስን ይችላል፡፡

### አንቀፅ 28. የድምፅ መስጫ ሰዓት

1. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ለማንኛውም ምርጫ የድምፅ መስጫ ሰዓት ከማለዳው 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ ይሆናል፡½

2. ቦርዱ የድምፅ መስጫ ሰዓቱን በተለየ ሁኔታ የወሰነ እንደሆነ የተወሰነውን የድምፅ መስጫ ሰዓት መራጩ ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች በይፋ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ቦርዱ የምርጫውን ነፃና ፍትሀዊነት ይበልጥ ያረጋግጣል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰዓቱ እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 29. ለመራጮች ስለሚሰጥ ገለፃ

1. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ወይም እሱ የሚመድበው የምርጫ አስፈፃሚ መራጮች ድምፅ ለመስጠት ሲመጡ ስለድምፅ አሰጣጡ ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ወይም እሱ የሚመድበው የምርጫ አስፈፃሚ መራጮችን እንደአመቺነቱ ከፍሎ እያሰባሰበ ለዚሁ በተዘጋጀው ፖስተር ላይ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት፡-

ሀ. የዕጩዎችን ሙሉ ስም ከነአያታቸው

ለ. የመወዳደሪያ ምልክቶቻቸውን ትክክለኛ መጠሪያ

ሐ. በፖለቲካ ድርጅት የተወከሉትንና በግል የቀረቡትን ዕጩዎች

መ. እያንዳንዱ ዕጩ ለየትኛው ምክZ ቤት አባልነት እንደሚወዳደር

ለመራጮች በግልፅ ማብራራት አለበት፡፡

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ወይም እሱ የሚመድበው የምርጫ አስፈፃሚ ዕጩዎችን ለማስተዋወቅ በሚያደርገው ገለፃ፡-

ሀ. የሁሉንም ዕጩዎች ስምና ምልክ} አንድም ሳያስቀርና ሳያጓድል

ለ. ስለማንኛውም ዕጩ ምልክ} አገልግሎትም ሆነ ሌላ ሁኔታ ዝርዝር ማብራሪያ ሳይሰጥና

ሐ. ማንኛውንም ዕጩ የመደገፍ ምልክትም ሆነ ሌላ አይነት እንቅስቃሴ ሳያደርግ

ሁሉንም እጩዎች በእኩልነት የማስተዋወቅ ግዴታ አለበት፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ መራጮች፡-

ሀ. ለጠቅላላ ምርጫ ሲሆን ሊመርጡ የፈለጉት ዕጩ ስም ወይም ምልክ} የሚገኝበት ባለ አራት ማዕዘን ቦታ ላይ፣

ለ. ለአካባቢ ምርጫ ሲሆን ሊመርጡ በፈለጉት ዕጩ ወይም ፓርቲ ምልክ} ፊት ለፊት በሚገኘው ባለአራት ማዕዘን ክፍት ቦታ ላይ

የ ( ወይም የጣት አሻራ ምልክ} በማድረግ መምረጥ እና ምልክy ወደውስጥ ሆኖ የድምፅ መስጫ ወረቀቱን በማጠፍ ኮሮጆ ውስጥ መክተት እንደሚገባቸው በግልፅ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

5. ምርጫው ከአንድ በላይ ለሆኑ ምክZ ቤቶች የሚደረግ ሲሆን

ሀ. ለእያንዳንዱ ምክZ ቤት የተዘጋጀውን የድምፅ መስጫ ወረቀት እና የቀለም አይነት

ለ. ለእያንዳንዱ ምክZ ቤት አንድ መራጭ ለስንት ዕጩ ድምፅ መስጠት እንደሚገባው ማብራራት እና ለእያንዳንዱ ምክZ ቤት አንድ አንድ የድምፅ መስጫ ወረቀት እንደሚሰጣቸው

ማስረዳት አለበት፡፡

6. ማንኛውም መራጭ ድምፅ ሲሰጥ የድምፅ መስጫ ወረቀቱ የተበላሸበት እንደሆነ የተበላሸውን በመመለስ ሌላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ሊሰጠው እንደሚችል ሊገለፅለት ይገባል፡፡

**አንቀፅ 30. መራጮችን በየተመዘገቡበት መዝገብ ለይቶ ስለማስተናገድ**

የምርጫ አስፈፃሚው፡-

1. መራጮች ገለፃውን ከተከታተሉ በኋላ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዳቸው ላይ የተመዘገቡበትን የመራጮች መዝገብ ቁጥር በመለየት ስማቸው ወደሚገኝበት መዝገብ ሹም ይልካል፡፡
2. የመዝገብ ሹሞቹም የመራጩን ማንነት ካቀረበው ማስረጃ ጋር በማመሳከር በየተራ እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 31. ድምፅ ለመስጠት ብቁ ስለመሆን

1. ማንኛውም መራጭ ድምፅ መስጠት የሚችለው በተመዘገበበት ምርጫ ጣቢያ በአካል በመገኘት ብቻ ነው፡፡
2. በማኛውም ሁኔታ በውክልና ድምፅ መስጠት አይፈቀድም፡፡
3. ድምፅ ለመስጠት በተመዘገበበት የምርጫ ጣቢያ የተገኘ መራጭ፡-

ሀ. የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ያለው

ለ. የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ የሰፈረ

ሐ. ድምፅ ያልሰጠ

መሆኑ ሲረጋገጥ ድምፁን በነፃነት የመስጠት መብት አለው፡፡

4. የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ የጠፋበት መራጭ ጉዳዩን ለምርጫ ጣቢያው በማመልከት በምርጫ ጣቢያው ነዋሪ መሆኑን እና በመዝገቡ ላይ ስሙ የሰፈረና ያልመረጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ጉዳዩ በቃለ ጉባኤ ተይዞ እንዲመርጥ ሊደረግ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 32. አንድ ጊዜ እና አንድ ቦታ ብቻ ድምፅ ስለመስጠት

1. ማንኛውም መራጭ በአንድ ቀን ለሚካሄድ ምርጫ ድምፅ ሊሰጥ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

2. በዕለቱ የሚካሄደው ምርጫ ከአንድ በላይ ለሆኑ የምክZ ቤት መቀመጫዎች ሲሆን መራጩ በተለያዩ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በአንድ ጊዜ እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

3. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሁሉም መራጮች በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ ድምፃቸውን ይሰጣሉ፡፡

**አንቀፅ 33. ድጋፍ ስለሚፈልጉ መራጮች**

1. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አዛውንቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ነፍሰጡሮችንና የመሳሰሉትን ቅድሚያ በመስጠት ድምፅ እንዲሰጡ ማድረግ አለበት።

2. በድምፅ አሰጣጡ ሂደት ራሱን ለመግለፅ፣ ምልክ} ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደኮሮጆ ለመክተት ዕርዳታ የሚያስፈልገው መራጭ ራሱ የመረጠውን ሰው ይዞ የመምጣት መብት አለው፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 በድጋፍ ፈላጊው የተመረጠው ሰው፡-

ሀ. ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

ለ. ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም የዕጩ ወኪል መሆን የለበትም።

4. ድጋፍ ሰጪው የመራጩን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ማክበር ይጠበቅበታል፡፡

**አንቀፅ 34. ምዝገባን ስለማጣራት**

1. ማንኛውም መራጭ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱን ለተመዘገበበት የመዝገብ ሹም በማቅረብ ስሙ በመዝገቡ ላይ እንዲታይለት ይጠይቃል፡፡

2. የመዝገብ ሹሙ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱ በምርጫ ጣቢያው የተሰጠ መሆኑንና የመራጩን ማንነት በማጣራት በካርዱ ላይ በተመዘገበው ተራ ቁጥር መሰረት ሙሉ ስሙ በመዝገቡ ላይ በትክክG መስፈሩንና ድምፅ ያልሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ በስሙ

ትይዩ ለፊርማ በተዘጋጀው የምርጫው ዕለት የፊርማ አምድ ላይ እንዲፈርም ተደርጎ ካርዱ ተቀዶ ይጣላል፡፡

3. የአካባቢ ምርጫ በሳምንት ልዩነት የሚካሄድ ከሆነ በመጀመሪያው ምርጫ ለመምረጡ በመዝገቡ ላይ የመጀመሪያው ሳምንት የምርጫው ዕለት ፊርማ አምድ ላይ እንዲፈርም ተደርጎ በካርዱ ግርጌ ለዚሁ በተዘጋጀው ቦታ ላይ የ( ምልክ} በማድረግ ይመልስለታል።

4. በሁለተኛው ሳምንት በሚካሄደው ምርጫ ድምፅ ከሰጠ በኋላ ካርዱ ተቀዶ ይጣላል፡፡

**አንቀፅ 35. ድምፅ መስጠቱን የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም በመቀባት ማረጋገጥ**

1. መራጩ በመዝገቡ ላይ ከፈረመ በኋላ ድምፅ መስጠቱን የሚያረጋግጥ ቀለም በአውራ ጣቶቹ ወይም በሌሎች ጣቶቹ ላይ አለመኖሩን በማረጋገጥ አውራ ጣቱን፣ አውራ ጣት የሌለው ከሆነ ማንኛውንም ሌላ ጣት በተዘጋጀው ቀለም እንዲቀባ ይደረጋል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም መራጩ ጣት የሌለው ከሆነ የምርጫ አስፈፃሚዎች አለመምረጡን በማረጋገጥ እንዲመርጥ ያደርጋሉ።

3. የእጆቹን ጣቶች ለምርጫ አስፈፃሚው ለማሳየት ወይም ቀለም ለመቀባት ፈቃደኛ ያልሆነ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት አይሰጠውም፣ መምረጥም አይችልም፡፡

4. ለአቅመ ደካሞች ወይም ድጋፍ ለሚፈልጉ መራጮች ድጋፍ ለመስጠት አብረው የመጡ ሰዎች ድምፅ የሚሰጡ ካልሆነ በስተቀር ጣታቸውን ቀለም አይቀቡም።

**አንቀፅ 36. የድምፅ መስጫ ወረቀት ስለመስጠት**

1. ከላይ በአንቀጽ 34 እና 35 መሠረት ተገቢው ሂደት ከተፈፀመ በኋላ ለመራጩ ለምርጫ ጣቢያው ከተዘጋጀው የድምፅ መስጫ ወረቀት ለአንድ ምክZ ቤት አንድ የድምፅ መስጫ ወረቀት ይሰጠዋል።

2. በዕለቱ የሚካሄደው ምርጫ ከአንድ በላይ ለሆኑ ምክZ ቤቶች ሲሆን ከየምክZ ቤቱ ምርጫ አንድ አንድ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ይሰጠዋል፡፡

## አንቀፅ 37. ወደሚስጥር ክፍል ስለመግባት

1. የድምፅ መስጫ ወረቀቱን የተቀበለ መራጭ ከማንም እይታ በተከለለው የሚስጥር ክፍል በመግባት ድምፅ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

2. ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መራጮች በአንቀፅ 33 መሠረት ከመረጧቸው ሰዎች ጋር ሚስጥር ክፍል በመግባት ድምፅ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

3. በንዑስ አንቀፅ 2 ከተጠቀሰው በስተቀር መራጩ ወደ ሚስጥር ድምፅ መስጫው ገብቶ ድምፅ በመስጠት ላይ እያለ ማንም ሰው በምንም ሁኔታ ተከትሎ ወይም ተደርቦ መግባት አይችልም፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሚስጥር ድምፅ መስጫ ቦታ ላይ የተቀመጡ እስክሪብቶ እና መርገጫዎች በተገቢው ሁኔታ መኖራቸውን እና ሌሎች የተከለከሉ የቅስቀሳ ጽሑፎች አለመለጠፋቸውን ወይም አለመቀመጣቸውን መራጮች ድምፅ በማይሰጡበት ክፍተት በየተወሰነ ጊዜ እየገባ ያረጋግጣል፡፡

## አንቀፅ 38. የድምፅ መስጫ ሳጥን ኮሮጆ ውስጥ ድምፅ መስጫ ወረቀት ስለመክተት

መራጩ በአግባቡ ድምፅ የሰጠበትን የድምፅ መስጫ ወረቀት በማጠፍ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ ዕይታ በግልፅ ስፍራ በተቀመጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን ወይም ኮሮጆ ውስጥ በመክተት ከምርጫ ጣቢያው ይወጣል፡፡

## አንቀፅ 39. ስለተበላሸ የድምፅ መስጫ ወረቀት

1. መራጩ የተሰጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በአግባቡ ሳይጠቀምበት የቀረ ወይም የተበላሸበት እንደሆነ ሁኔታውን ለምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በማስረዳት ሌላ የድምፅ መስጫ ወረቀት እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊም ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰውን የተበላሸ የድምፅ መስጫ ወረቀት እንዲመለስ በማድረግ በጀርባው ላይ "የተበላሸ" የሚል ወይም ሌላ ምልክ} አድርጎ በምትኩ ሌላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ለመራጩ መስጠት አለበት፡፡

3. የተበላሸው የድምፅ መስጫ ወረቀት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ወይም ቦታ እንዲቀመጥ ያደርጋል።

**አንቀፅ 40. ድምፅ የመስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑ**

1. የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በተለያየ ምክንያት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን የተቋረጠ እንደሆነ

ሀ. የድምፅ አሰጣጡን ሂደት እንዲቋረጥ ያደረገው ሁኔታ መስተካከሉ ወይም መወገዱ በምርጫ አስፈጻሚዎች ከታመነበት እና

ለ. ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ከተያዘ በኂላ

የተቋረጠው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ሊቀጥል ይችላል፡፡

3. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት የተቋረጠበት ሁኔታ ከአቅም በላይ ከሆነ እና ሊስተካከል ካልቻለ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ባለበት እንዲቆም ይደረጋል፡፡

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ሁኔታ ለቦርዱና በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች ሪፖርት ይደረጋል፡፡

5. የተቋረጠው የድምፅ አሰጣጥ ቦርዱ በሚወስነው መሠረት በሌላ ጊዜ ይካሄዳል።

**አንቀፅ 41. ድምፅ መስጠትን ስለመቃወም**

1. ማንኛውም መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት የእጩ ተወካይ ድምፅ በመስጠት ሂደት ላይ ያለው ሰው የመራጭነት መብት የሌለው ወይም በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት ያልተመዘገበ ነው በማለት ሊቃወም ይችላል።

2. አንድ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ቢከለከል እራሱ ወይም ከእጩ ተወካዮች አንዱ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል።

3. የእጩ ተወካይ ወይም መራጩ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ከተደነገጉት መቃወሚያ ነጥቦች ውጭ በሆነ በማኛቸውም የምርጫ አስፈፃሚ የእጩ ተወካይ ወይም በሌላ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በተገኘ ሰው አግባብ ያልሆነ ድርጊት ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ የቀረበውን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል ውሳኔውን ያሳውቃል፡፡

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በዚህ አንቀፅ መሠረት የቀረቡ ቅሬታዎችንና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ መልሶችን የጽሁፍ ሰነድ በመረጃነት ይይዛል፡፡

## አንቀፅ 42. ስለጊዜያዊ ድምፅ

1. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ድምፅ እንዳይሰጥ ተቃውሞ የቀረበበት ሰው ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ የወሰነ እንደሆነ ለዚሁ በተዘጋጀው ፖስታ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

2. የተሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ቦርዱ ባወጣው ደንብ ቁጥር 1/2000 መሰረት በሚሰጠው ውሣኔ መሰረት በቆጠራ ሊካተት ወይም ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

3. ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ በደንቡ መሰረት የመምረጥ መብት ያለው መሆኑን የድምፅ ማዳመር እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ በቆጠራ አይካተትም፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ስለድምፅ አሰጣጥ መጠናfk

## አንቀፅ 43. የምርጫ ጣቢያ መዘጋት

1. የድምፅ መስጫው ሰዓት ሲጠናቀቅ የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የምርጫ ጣቢያ እንዲዘጋ ያደርጋል።

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው ተራ ሲጠብቁ ወይም ስለምርጫው የሚሰጠውን ገለፃ ሲከታተሉ የነበሩ መራጮች ድምፅ እንዲሰጡ መደረግ አለበት።

3. ድምፅ አሰጣጡ ተጠና የምርጫ ጣቢያው ከተዘጋ በኋላ ከምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ከህዝብ ታዛቢዎች፣ ከተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች፣ ከተፈቀደላቸው ተንቀሳቃሽ የዕጩ ወኪሎች እና የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም።

4. የምርጫ ጣቢያው ፀጥታ አስከባሪዎች በመግቢያው በር ላይ በመሆን ጥበቃ ያደርጋሉ።

## አንቀፅ 44. የድምፅ መስጫ ሳጥን ወይም ኮሮጆ ስለመቆለፍ እና ስለሚደረግ ጥንቃቄ

1. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንደተጠናቀቀ እና የምርጫ ጣቢያው እንደተዘጋ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፣

   ሀ. የህዝብ ታዛቢዎች፣

   ለ. ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች እና

   ሐ. የምርጫ አስፈፃሚዎች

   በግልፅ በሚያዩበት ሁኔታ ኮሮጀው ከተሰቀለበት ሳይወርድ የላይኛው ባለ አንድ ዚፕ የኮሮጆ ክፍል በቢጫው ቁልፍ ይቆልፋል።

2. ኮሮጆው የተቆለፈበት ቢጫ ቁልፍ ቁጥር እንዲመዘገብ ይደረጋል።

3. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት የውሎ ሁኔታ በዝርዝር ተገልፆ በቃለ ጉባኤ እንዲያዝ ይደረጋል።

4. ለድምፅ መስጫ ኮሮጆውና ለ&ሎች የምርጫ ቁሳቁሶች አስፈላጊው ጥበቃና ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

## ክፍል ሦስት
## ስለድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ
## ምዕራፍ አንድ
## ስለድምፅ ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት

### አንቀፅ 45. የድምፅ ቆጠራ ቦታ

1. በማንኛውም ደረጃ ምርጫ የድምፅ ቆጠራ የሚከናወነው ድምፅ በተሰጠበት የምርጫ ጣቢያ ነው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ በሆነ ምክንያት፡-

   ሀ. በምርጫ ጣቢያው ቆጠራ ለማካሄድ የማይቻል ከሆነ የተፈጠረውን አስገዳጅ ሁኔታ የምርጫ ጣቢያው ለምርጫ ክልሉ በመግለፅ ጥያቄ አቅርቦ ሲፈቀድ ወይም

   ለ. የምርጫ ክልሉ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ ውሣኔ ሲያሳልፍ

   ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ሊካሄድ ይችላል፡፡

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራው በምርጫ ክልሉ እንዲካሄድ ያስፈለገበትን ምክንያት በመግለፅ ጥያቄውን ለምርጫ ክልሉ የሚያቀርበው በምርጫ ጣቢያው ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ውሣኔ መሆን አለበት፡፡

4. የምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን ውሣኔ የሚሰጠው በምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይሆናል፡½

5. የቆጠራ ቦታ ለመለወጥ የተደረጉት ስብሰባዎች ቃለጉባኤ ተይዞ ለበላይ የምርጫ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

6. የድምፅ ቆጠራ በምርጫ ክልል እንዲካሄድ ሲወሰን የምርጫ ጣቢያው የህዝብ ታዛቢዎችና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በምርጫ ክልሉ በመገኘት የቆጠራውን ሂደት ይከታተላሉ፡፡

7. የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች የድምፅ ቆጠራውን ያከናውናሉ፡፡

8. የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ ቆጠራው አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## አንቀፅ 46. የድምፅ መቁጠሪያ ቦታ ስለማዘጋጀት

1. የድምፅ መቁጠሪያ ቦታው የህዝብ ታዛቢዎችና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በቅርበት እያዩ ለመከታተል በሚችሉበት ሁኔታ በቂ ብርሃን ያለበት ምቹ ቦታ ተመርጦ ይዘጋጃል፡፡

2. የህዝብ ታዛቢዎችና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በቆጠራው ቦታ እንዲገኙ ሰዓቱን እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የህዝብ ታዛቢዎችና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች ባሉበት የድምፅ መስጫው ኮሮጆ ከተንጠለጠለበት ቦታ በጥንቃቄ በማውረድ ለሁሉም በሚታይ መልኩ ለቆጠራ በተዘጋጀው ቦታ ያስቀምጣል፡፡

## አንቀፅ 47. ድምፅ የሰጡ መራጮችን በመራጮች መዝገብ ላይ ስለመቁጠር

1. የመራጮች መዝገብ ላይ የድምፅ መስጫው ዕለት የመራጩ ፊርማ በሚለው አምድ ስር የፈረሙትን ድምፅ የሰጡ መራጮች አንድ በአንድ በግልፅ በመቁጠርና በማዳመር ቁጥሩ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡
2. በመራጮች መዝገብ ላይ ከተመዘገበው ህዝብ ብዛት ላይ በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮችን ቁጥር በመቀነስ ድምፅ ያልሰጡትን ብዛት እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

3. በዕለቱ ተበላሽተው የተመለሱ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለብቻ ተቆጥረው ይመዘገባሉ፡፡

4. በዕለቱ ተርፈው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረው ይመዘገባሉ፡፡

5. በዚህ አንቀፅ የሚደረገው ቁጥጥር የህዝብ ታዛቢዎችና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በግልፅ በሚያዩበትና በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ አማካኝነት መከናወን ይኖርበታል፡፡

6. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፡-

ሀ. ለምርጫ ጣቢያው የመጣውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት፣

ለ. የተበላሸውን ብዛት፣

ሐ. ሥራ ላይ ያልዋለውን ብዛት፣

መ. ቀሪውን ወይም ድምፅ የተሰጠበትን ብዛት

በይፋ በመግለፅ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

7. ከዚህ በላይ የተዘረዘረው የቁጥጥር ሂደት ምርጫው ከአንድ በላይ ለሆኑ ምክZ ቤቶች የሚካሄድ ሲሆን ለየምክZ ቤቱ የተላኩት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለየብቻ ተቆጥረው በየተራ እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡

**አንቀፅ 48. የድምፅ መቁጠሪያ ሰነድ እና ቁሳቁስ ስለማዘጋጀት**

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለቆጠራው ተግባር ከቦርዱ የተላኩለትን፡-

1. የድምፅ ቆጠራ ውጤት ማስተላለፊያ፣
2. የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለሕዝብ ማሳወቂያ
3. የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ፣
4. የመተማመኛ ሰነድ፣
5. እስክሪቢቶ እና የመሳሰሉትን

አንድ በአንድ በመቁጠር ለቆጠራ ዝግጁ ያደርጋል፡፡

**አንቀፅ 49. ለምርጫ አስፈፃሚዎች ሥራ ማከፋፈል**

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ እንደምርጫው አይነት ለምርጫ አስፈፃሚዎች ያከፋፍላል።

2. ሌሎች የቆጠራ ተግባራትን በምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል።

3. ድምፅ ለማን እንደተሰጠ ከድምፅ መስጫ ወረቀቱ ላይ አንድ በአንድ እያረጋገጠ ለቆጣሪዎች የሚነግረው የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ነው።

4. የህዝብ ታዛቢዎችና የዕጩ ወኪሎች የቆጠራውን ሂደት ከመከታተል ወይም ቅሬታ ካለ ከማቅረብ ውጪ በቆጠራው ተግባር ውስጥ መሣተፍ የተከለከለ ነው።

**አንቀፅ 50. ስለድምፅ ቆጠራው አፈፃፀም ገለፃ ስለመስጠት**

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ስለድምፅ ቆጠራው አፈፃፀም ለምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ለህዝብ ታዛቢዎች እና ለተቀማጭ የእጩ ወኪሎች ገለፃ ይሰጣል። በገለፃውም፡-

1. ቆጠራው ለየምርጫው ዓይነት በተራ በተራ የሚከናወን መሆኑን፣

2. በእያንዳንዱ ድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ የተሰጠው ድምፅ ለማን እንደሆነ የሚገለፅ መሆኑን፣

3. ለምርጫ አስፈፃሚው የሚሰጠውን የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ አሞላል እና አቆጣጠር የህዝብ ታዛቢዎች እና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች ሊከታተሉ በሚችሉበት ምቹ ቦታ መቀመጥ እንዳለበት፣

4. በድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዡ ላይ የሰረዝ ቆጠራ (ታሊ) እንዴት እንደሚከናወን፣

5. የድምፅ ቆጠራ ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት የተጠናቀቀ መሆኑን፣

6. በቦርዱ ውሣኔ ካልሆነ በስተቀር የድምፅ ቆጠራ ከተጀመረ በኋላ ሊቋረጥ ወይም ሊቆም የማይችል መሆኑን

በይፋ ማስረዳት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለድምፅ ቆጠራ አጀማመርና ሂደት

### አንቀፅ 51. ቆጠራ ስለመጀመር

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የቆጠራው ቅድመ ዝግጅት የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ የድምፅ ቆጠራው መጀመሩን በቦታው ለተገኙት የህዝብ ታዛቢዎች እና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በይፋ ይገልፃል፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የድምፅ ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫው ሳጥን ወይም ኮሮጆ:-

   ሀ. ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት የጎኑ የኮሮጆ ባለሁለት ዚፕ ክፍል በአረንጓዴው ቁልፍ በታሸገበት ሁኔታ ያልተሰበረ መሆኑን፣

   ለ. ድምፅ ከተሰጠ በኋላ የኮሮጆው የላይኛው ባለአንድ ዚፕ በቢጫ ቁልፍ በታሸገበት ሁኔታ ያልተሰበረ መሆኑን

   ሐ. ያልተከፈተ፣ ያልተቀደደ ወይም ብልሽት ያልደረሰበት መሆኑን፣

   መ. የአረንጓዴው ቁልፍ ቁጥር ጠዋት ከተመዘገበው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን

   ለሕዝብ ታዛቢዎችና ለዕጩ ወኪሎች በማሳየትና ቃለጉባኤ በመያዝ አረንጓዴውን ቁልፍ በጥንቃቄ ይሰብራል፡፡

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ድምፅ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች በሙሉ ከድምፅ መስጫ ኮሮጆ ውስጥ

በማውጣት ኮሮጀው ባዶ መሆኑን በግልፅ እንዲታይ ወይም እንዲፈተሽ እና እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 52. የድምፅ መስጫ ወረቀት ስለመለየት እና የቆጠራ ቅደም ተከተል

1. የምርጫ አስፈፃሚዎች የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በመዘርጋት ድምፅ በተሰጠባቸው የምክZ ቤት አይነት በመለየት ለየብቻ እንዲቀመጡ ያደርጋሉ።

2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የድምፅ መስጫ ወረቀቶቹ ጀርባ ላይ ያለው ፊርማ እና ማህተም በማየት በምርጫ ጣቢያው የተሰራጩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

3. ምርጫው የተካሄደው ከአንድ በላይ ለሆኑ ምክZ ቤቶች የሆነ እንደሆነ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር፦

   ሀ. ለጠቅላላ ምርጫ መጀመሪያ የህዝብ ተወካዮች ምክZ ቤት በመቀጠል የክልል ምክZ ቤት ድምፅ ይቆጠራል፡፡

   ለ. ለአካባቢ ምርጫ ለዞን፣ ለወረዳ፣ ለከተማ፣ ለማዘጋጃ ቤት፣ ለክፍለ ከተማና ለቀበሌ ምክZ ቤቶች የተሰጡ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች እንደ ቅደም ተከተላቸው ይቆጠራሉ፡፡

   ሐ. የጠቅላላ ምርጫ ማሟያ ከአካባቢ ምርጫ ጋር የተካሄደ እንደሆነ በመጀመሪያ የጠቅላላ ምርጫ ማሟያ በመቀጠል የአካባቢ ምርጫ ቆጠራ ከላይ በሀ እና በለ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት ይከናወናG½½

4. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለሁሉም ምክZ ቤቶች አይነት የተሰጠውን ድምፅ ለብቻ በመለየት ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3 በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት ለአንዱ ምክZ ቤት የተሰጠው ድምፅ በሙሉ ተቆጥሮ ሲጠናቀቅ የሚቀጥለውን በመቁጠር ቆጠራውን ተራ በተራ በጥንቃቄ ማከናወን አለበት፡፡

## አንቀፅ 53. የድምፅ ቆጠራ ሂደት

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቅድሚያ የሚቆጠረውን የምክZ ቤት አይነት ካሳወቀ በኋላ ለዚሁ ምክZ ቤት ድምፅ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች ብቻ ለይቶ ለቆጠራ ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቅድሚያ የሚቆጠረውን ምክZ ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ውስጥ አንዱን ብቻ በማንሳት፡-

   ሀ. የዕጩዎቹ ምልክቶች ባሉበት በኩል ፊት ለፊት ለህዝብ ታዛቢዎችና ለተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች በቅርበት ያሳያል።

   ለ. መራጩ ድምፅ የሰጠው ለየትኛው ዕጩ እንደሆነ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገራል፡½

3. ድምፅ የተሰጠበት የድምፅ መስጫ ወረቀት ዋጋ ያለውና ለተባለው ዕጩ በትክክG ድምፅ የተሰጠበት መሆኑን በጋራ ስምምነት ሲደረስበት የዕጩው ስም የተመዘገበበት ሰንጠረዥ ላይ እንዲመዘገብ ያደርጋል፡፡ በዚሁ መሠረት ቆጠራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ይከናወናG½½

4. ድምፅ የተሰጠው ምክZ ቤት መቀመጫ ብዛት አንድ ከሆነ ለእያንዳንዱ ዕጩ ድምፅ የተሰጠበት ወረቀት ለየብቻ ይቀመጣል።

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እያንዳንዱ ቆጠራ ሲጠናቀቅ ቆጠራው የሚከናወንበት ምክZ ቤት ድምፅ መስጫ ወረቀት በሙሉ መቆጠሩን በማረጋገጥና ታዛቢዎችና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎችም እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

6. ሰንጠረዡን የመዘገበው የምርጫ አስፈፃሚ ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጠው ድምፅ ጠቅላላ ብዛት በማዳመር ተራ በተራ ይገልፃል፡፡

7. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 6 የተጠቀሰው የቆጠራ ውጤት ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፡-

   ሀ. ለጠቅላላ ምርጫ እንደየምርጫው ዓይነት ለየብቻ ተለይቶ የተቀመጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በመቁጠር፣

ለ. ለአካባቢ ምርጫ ከድምፅ መስጫ ወረቀቱ ላይ ምልክቶቹን ለይቶ በመቁጠር

እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

8. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቆጠራው ውጤት ላይ የሁሉም ስምምነት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

9. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቆጠራው ሰንጠረዥ ላይ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የህዝብ ታዛቢዎችን እና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎችን በማስፈረም የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዡን ይረከባል፡፡

10. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የአንዱ ምክZ ቤት የድምፅ ቆጠራ ሲጠናቀቅ ቆጠራው መጠናቀቁንና የሚቀጥለው ቆጠራ የሚጀመር መሆኑን ለሁሉም ማሳወቅ አለበት፡፡

11. ለሁሉም ምክZ ቤቶች ድምፅ የተሰጠበት ወረቀት ከላይ በተጠቀሰው ዝርዝር መሠረት በየተራ ተቆጥሮ አስፈላጊው ሰነድ ተሞልቶና ቃለጉባኤ ተይዞ በዕለቱ በቆጠራው የተገኙት የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች እና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች እንዲፈርሙበት መደረግ አለበት፡፡

## አንቀፅ 54. ስለዋጋ አልባ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች

1. ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ዋጋ አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

ሀ. የመራጩ ማንነት በስም የተገለፀበት ከሆነ፣

ለ. ከተመራጮች ቁጥር በላይ ምልክ} የተደረገበት ከሆነ፣

ሐ. ምንም ምልክ} ያልተደረገበት ከሆነ፣

መ. መራጩ ማንን እንደመረጠ መለየት የሚያስቸግር ከሆነ፣

ሠ. ህጋዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት ያልሆነ ወይም በምርጫ ጣቢያው ያልተሰራጨ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ፡፡

2. ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአንዱ ዋጋ አልባ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች "ውድቅ" የሚል ፅሁፍ በጀርባቸው ተጽፎበት ለብቻቸው ተቆጥረው ይታሸጋሉ፡፡

## አንቀፅ 55. ቅጾችን ለይቶ ስለመሙላት

1. የእያንዳንዱ ምክZ ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀት ለየብቻ ተለይቶ ከተቆጠረ በኋላ፡-

   ሀ. የምርጫ ጣቢያውን የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለምርጫ ክልል ማሳወቂያ ቅጽ፣

   ለ. ለዕጩ ወይም ለወኪሉ የሚሰጥ የድምፅ ቆጠራ ውጤት መተማመኛ ቅጽ፣

   ሐ. የምርጫ ጣቢያ የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለሕዝብ ማሳወቂያ ቅጽ፣

   መ. በቦርዱ የተላኩ ሌሎች ቅጾች፣

በአግባቡ ተሞልተው የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የህዝብ ታዛቢዎች እና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች እንዲፈርሙበት ይደረጋል።

2. የሁሉም ምክZ ቤቶች አባላት ምርጫ የድምፅ ቆጠራ ውጤት አሞላሉ ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት በየተራ መከናወን አለበት፡፡

## አንቀፅ 56. የተቆጠሩ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን እና ሰነዶችን ስለመለየት

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለእያንዳንዱ ምክZ ቤት የሚደረገው የድምፅ ቆጠራ ሲጠናቀቅ፡-

   ሀ. ዋጋ ያላቸው ድምፅ በአግባቡ የተሰጠባቸውን፣

   ለ. ዋጋ አልባ የሆኑትን፣

   ሐ. ተበላሽተው በመራጭ የተመለሱትን፣

   መ. ድምፅ ያልተሰጠባቸውን ወይም የተረፉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለየብቻው ታስሮ

ሠ. ለእያንዳንዱ ምክZ ቤት ድምፅ የተቆጠረበት መቁጠሪያ ሰንጠረዥ፣

ረ. ሁለቱም የመራጮች መዝገቦች

በድምፅ መስጫ ኮሮጆ ውስጥ ያስቀምጣል።

**አንቀፅ 57. የድምፅ ቆጠራ የማይቋረጥ ስለመሆኑ**

የማንኛውም ምርጫ የድምፅ ቆጠራ በቦርዱ ውሣኔ ካልሆነ በስተቀር ሊቆም ወይም ሊቋረጥ አይችልም።

**አንቀፅ 58. ስለድምፅ ቆጠራ መጠናfk**

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የተለያዩ ቅጾችና ሰነዶች ተሞልተው መጠናቀቃቸውን ካረጋገጠ በኋላ ቆጠራው መጠናቀቁን ያበስራል።

2. በወቅቱ በቆጠራው ሂደት የተገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች እና ተቀማጭ የዕጩ ወኪሎች፡-

ሀ. አጠቃላይ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት፣

ለ. የድምፅ ቆጠራው ሂደት፣

ሐ. የምርጫው ውጤት

በትክክG የተካሄደ ስለመሆኑ በተዘጋጀው የመዝጊያ ቃለጉባኤ እና የምርጫ ውጤት መተማመኛ ቅፅ ላይ ይፈራረማሉ።

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እያንዳንዱን ተቀማጭ የዕጩ ወኪል በማስፈረም የድምፅ ቆጠራ ውጤቱን ወዲያውኑ ይሰጣል።

4. ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም በድምፅ አሰጣጡ፣ በቆጠራው ወይም በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው ተቀማጭ የዕጩ ወኪል ቅሬታውን በምርጫ ጣቢያው ሊያስመዘግብ ይችላል።

**አንቀፅ 59. የድምፅ ቆጠራ ውጤትና የምርጫ ቁሳቁስ ስለመላክ**

በየምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ምርጫ የተከናወነባቸው፡-

1. የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለየብቻ ተለይተው፣
2. የመራጮች መዝገቦች፣
3. የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ በኮሮጆው ውስጥ እንደታሸጉ፣
4. ያልተቆጠሩ ጊዜያዊ ድምፅ የተሰጠባቸውን ፖስታዎች እንደታሸጉ፣
5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የየምርጫውን ዓይነት የቆጠራ ውጤት ማሳወቂያ ቅፅ 07 እና የመክፈቻ እና መዝጊያ ቃለጉባዔዎች በፖስታ እንደታሸጉ፣
6. ልዩ ልዩ የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች

በፀጥታ አስከባሪዎች በማሳጀብ ወደምርጫ ክልል ማድረስ አለበት።

## ምዕራፍ ሦስት

## የድምፅ ቆጠራ እናማዳመር ውጤት አገላለፅ

### አንቀፅ 60. የድምፅ ቆጠራ እና ማዳመር ውጤት አገላለፅ ሂደት

1. በምርጫ ጣቢያ የሚገለፅ የድምፅ ቆጠራ ውጤት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያ የተለያዩ ቦታዎች ለዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ ተሞልቶ ለሕዝብ በይፋ ይገለፃል።

2. በምርጫ ክልል የሚገለፅ የድምፅ ማዳመር ውጤት የየምርጫ ጣቢያው የድምፅ ቆጠራ ውጤት ተጠና እንደደረሰ ዕጩዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት ውጤቱን በማዳመር የተገኘውን ውጤት ለዚሁ በተዘጋጀው ቅፅ ተሞልቶ በምርጫ ክልሉ እና በየምርጫ ጣቢያዎቹ በተለያዩ አካባቢዎች በመለጠፍ ለህዝብ እንዲገለፅ ይደረጋል።

3. በተሻሻለው የምርጫ ህግ አንቀፅ 95 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት የመምረጥ መብት እንዳለው

የሚገልፅ ውሣኔ ለምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ካቀረበ የሰጠው ድምፅ እንዲዳመር ይደረጋል፡፡

4. የምርጫ ክልሉ ኃላፊ፡-

ሀ. የምርጫውን ድምር ውጤት መተማመኛ ለዕጩዎች ወይም ለወኪሎቻቸው በማስፈረም መስጠት አለበት፡፡

ለ. የምርጫውን ድምር ውጤትና አጠቃላይ ሪፖርት ለቦርዱ ጽሕፈት ቤትና በየደረጃው ለሚገኙ የበላይ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መላክ አለበት፡፡

## አንቀፅ 61. አሸናፊውን ለመለየት ያልተቻለ እንደሆነ

በምርጫ ክልል ውጤት ከተደመረና ቅሬታዎች እልባት ካገኙ በኋላ ዕጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ ከፍተኛ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ ይካሄዳል፡፡

## አንቀፅ 62. የተመራጭነት መታወቂያ ወረቀት ስለመስጠት

በምርጫው አሸናዕ ለሆነው ዕጩ እንደምርጫው አይነት የተመራጭነት መታወቂያ ካርድ ለመስጠት በቦርዱ ስልጣን በተሰጠው የምርጫ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ተሞልቶ ይሰጠዋል፡፡

## አንቀፅ 63. በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚቀርብ ተቃውሞ

1. በድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ፣ ማዳመር እና ውጤት አገላለፅ ሂደት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ቦርዱ ባወጣው ደንብ ቁጥር 1/2000 ዓ.ም. መሰረት ውሣኔ ያገኛሉ፡፡

2. የምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያ ሀላፊዎች ለጽሕፈት ቤታቸው የቀረቡ ቅሬታዎችና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ ውሣኔዎችን ዋና ቅጂ እና የፅሑፍ ማስረጃዎችን ፋይል አድርገው መያዝ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 64. በቦርዱ ስለሚገለፅ የምርጫ ውጤት

1. ቦርዱ የጠቅላላ ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠቃሎ እስከሚደርሰው ድረስ ከየምርጫ ክልሉ የመጣለትን የምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. ቦርዱ የጠቅላላ ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠናl ሲደርሰው የምርጫውን አጠቃላይ ውጤት ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 65. ስለአካባቢ ምርጫ ውጤት አገላለፅ

1. ከላይ በአንቀፅ 64 ስለምርጫ ውጤት አገላለፅ የተደነገገው እንዳግባብነቱ ለአካባቢ ምርጫ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. ቦርዱ የአካባቢ ምርጫ ውጤት በክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በጊዜያዊነት እንዲገለፅ ሊያደርግ ይችላል።

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የአካባቢ ምርጫ ውጤት በክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሲጠቃለል አጠቃላይ የውጤቱ ሪፖርት ለቦርዱ መላክ ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 66. በቦርዱ ስለሚሰጥ ይፋዊ መግለጫ

1. የጠቅላላ ምርጫ ሂደት ተጠናl አስፈላጊ መረጃዎች ከተሰባሰቡ በኋላ ቦርዱ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል፡፡
   ሀ. በምርጫው የተመዘገቡ መራጮች ብዛት፣
   ለ. በምርጫው ድምፅ የሰጡ መራጮች ብዛት፣
   ሐ. በምርጫው ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ ተመዝጋቢ መራጮች በመቶኛ፣
   መ. የተመረጡ ዕጩዎች የስም ዝርዝር፣
   ሠ. የተመረጡ ዕጩዎች የምርጫ ክልልø
   ረ. የፖለቲካ ድርጅቶች ለየምክZ ቤቱ ያገኙት መቀመጫ ብዛት፣
   ሰ. ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ከጥቅም ውጭ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣

ሺ. እያንዳንዱ ዕጩ በየምርጫ ጣቢያ ያገኘው የድምፅ ውጤት እና ሌሎች መረጃዎች

ከምርጫ ክልሉ እንደደረሰውና አጠናk[ እንደጨረሰ ይፋ ያደርጋል፡፡

2. ቦርዱ የአካባቢ ምርጫ ሂደት ተጠናl እንደደረሰው እንደአግባብነቱ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ስር በተዘረዘረው መሠረት ይፋ ያደርጋል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 67. ስለተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀፅ 68. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከጥር 6 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡½

መርጋ በቃና (ፕሮፌሰር)

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ

ሰብሳቢ